# “ ቀለበቴን ስጧት ”

-፩-

ከበልጅግ አሊ

**አቤት አቤት ደስ ማለቱ፣ አቤት አቤት ደስ ማለቱ፣**
**ያ ምንደኛ ፣የኢሕአፓ ቅጥረኛ ፣**
**በቀይ ሽብር ተመትቶ ፣መንገድ ላይ ሲተኛ።**

**የፋሺሽቶች መዝሙር**
**1970**

የከርቸሌ ፍርደኛ ከወትሮው ለየት ያለ ሃዘን ሰፍሮበታል ። የወቅቱ አስከፊ ገፅታን የማይገነዘቡ የወንጀል እስረኞች እንኳን አዘውትረው ከሚያወሩት የሌብነት ገድል ተቆጥበዋል ። ምን ትሆን ይሆን ? የሚለው ጥያቄ በእያንዳንዱ እስረኛ አዕምሮ ውስጥ ይጉላላል።የልጅቷን የደስ ደስ የማያውቅ የለም ። ለባሏ ያላት ፍቅር ደግሞ የተደነቀና እያንዳንዱ እስረኛ ለራሱ የሚመኛት ዓይነት ሚስት ናት ። እሁድ እሁድ ሕፃን ልጃቸውን ታቅፋ ለጥየቃ ሰልፍ ለመያዝ በሌሊት ነው የምትደርሰው ። እሁድ ብዙ ምግብ ሰለሚመጣ የምግቡን ማምጣት የምታስተጓጉለው ሰኞ ሰኞ ነው ። እሱም በግድ በእሰረኛው ልመና ።

ባልና ሚስት ከአንድ ባሕር ይቀዳሉ እንዲባል እሱ ደግሞ በሃኪም ቤት በጣም የተወደደ ነው። ሃኪም ቤት ሰላችሁ ሌላ እንዳይመስላችሁ ። ከርቸሌ ውስጥ ያለውን ማለቴ ነው ።ከርቸሌ በዛ ወቅት በፍርደኛ ፣ በሴቶች ፣ በፍታብሄር፣ በአለም በቃኝ፣በሃኪም ቤትና በቀጠሮ ይከፋፈላል። ሃኪም ቤት የምለው ያንን ነው ። ጠያቂ ለሌላቸው ፣ ምግብ ከውጭ ለማይመጣላቸው እስረኞች ተሚጋች ነው። የመጣው ምግብ ለሁሉም ይከፋፈል ባይ ፣ ተወዳጅና አንደበተ ርቱዕ ነው ። ተናግሮ አይጠገብም ።

“ከተጋባን ገና ሁለት ዓመታችን ነው“ አለና ጀመረ። አንድ ቀን እንደ ድንገት ነበር የሕይወት ታሪኩን ያጫወተኝ ። “ገና ሳያት ነው የወደድኳት ። የተተዋወቅነው ኮመርስ ስትማር ነው ።አንድ ቀን ከሥራ ወጥቼ ወደ ብሔራዊ ቲያትር በእግሬ ስኳትን እንደ አጋጣሚ የጫማዋ ታኮ ተገንጥሎ ወደ ኋላ ቀርቶባት ስታነክስ ከኋላዋ እየሄድኩ ነበረና ታኮውን አንስቼ ሰጠኋት ።በእፍረት መልክ ከአንገቷ ጎንበስ አለችና ተቀበለችኝ። መሄድ አቃታት ልደግፍሽ እንዴ ? አልኳት ። ተግደረደረች ፣ እጄን እንድትይዝ ገፋፋኋት። ተሽኮረመመች ፣ውበቷ ይበልጥ ጨመረ ፤ ፈግግ አልኩ ፤ ፈገግ አለች ። የእሷን አላውቅም የእኔ ልብ ቀለጠ ። ስትፈራ ስትተባ እንደደገፍኳት ታክሲ መውሰጃው ጋ ደረስን ። መሄዷ ቅር አሰኘኝ ። አንድ ነገር ጠረጠርኩ ። ምን አልባት ገንዘብ አልያዘች ይሆን ? ጠየቅኋት ። ምንም መልስ አልሰጠችኝም ። ገንዘብ አወጣሁና ሰጠኋት ። አልቀበልም አለችኝ ። ግድ የለም ነገ ቴሌ ባር እጠብቅሻለሁ ትመልሽልኛለሽ አልኳት። በስንት ሰዓት አለችኝ ። እንደዛሬው ብያት ተለያየን ።

እንደዛ ቀን የረዘመብኝ ሌሊት የለም ። በበነጋታውም ቀኑ አልሄድ አለ ። ያ ቀርፋፋ ቀን አልቆ በቀጠሮው ሰዓት ቀድሜ ተገኘሁ ።አረፈደች ፣ ጨነቀኝ ፣ ደቂቃዎቹ እንደ ሰዓት ሆኑብኝ ። በሩቅ ከጓደኛዋ ጋር ስትመጣ አየኋት ። ከጓደኛዋ ጋር መምጣቷን አልወደድኩትም። ግን ጓደኛዋን ካስተዋወቀችኝ በኋላ ጓደኛዋን ይዛ የመጣችው እኔን ለማሳየትና የጓደኛዋን ምክር ለመቀበል እንደፈለገች ገመትኩ ። ጓደኛዋ ታየኛለች፣ በጥንቃቄ ታጠናኛለች ፣ እሷ አታየኝም ። እኔም ብሆን ዘንጬ ነበር የሄድኩት ። አጠገቤ ደረሱና ሰላምታ ተለዋወጥን ። ሻይ እንድንጠጣ ጋበዝኳቸው ። ጓደኛዋ እሄዳለሁ እቸኩላለሁ አለች ። አይሆንም ባይሆን ሻይም ቢሆን ቀምሰሽ ትሄጃለሽ አልኩ ።

እሺ አሉና ገባን ። ጨዋታ ቀጠለ በጥቂት ጊዜ ስለኔ ጠይቅው ጨረሱ ።ለወትሮው ሰለ ግል ሁኔታዬ የሚጠይቀኝን ባልወድም እውነቱን ተናገርኩ ።

ጓደኛዋ ለግብዣው አመስግናኝ እቸኩላለሁ ብላን ሄደች። ጨዋታ ተጀመረ ። ቤቷ በሰላም መድረሷን ፣ ሠፈሯ የት እንደሆነ ፣ ትምህርት እንዴት እንደሆነ አወራን ። በመሃል ገንዘብ አውጥታ ልትሰጠኝ ስትል ዛሬ አልቀበልም ነገ በዚሁ ሰዓት እዚሁ እንገናኝና ትሰጪኝአለሽ አልኳት ። ሰቃ እሺ አለችኝ ። በዛው ፍቅር ተጀመረ ። ቴሌ ባር ሁለተኛ ቤታችን ሆነ ። የምትኖርበት ድረስ መመላለስ ልምድ ሆነ ። ሥራ እሷን መሸኘት ከዛም ወደ ቤት መሄድ ተጀመረ ። ሕይወቴን ወደድኳት፣ ኑሮዬ ጣፈጭ ሆነ ፣ ለካስ ፍቅር እንዲህ ይጣፍጥ ነበር ብዬ በተደጋጋሚ አስብ ነበር ።ጊዜው እየረዘመ መጣ ትምህርቷን ጨርሳ ሥራ ያዘች ። ተረዳድተን ሰፋ ያለ ቤት ፈልገን ገባን ። ቤት ለማግኘት ዘመዶቿ ባይረዱኝ አልችልም ነበር ።

ቤተሰቦቿ ካልተጋባችሁ አንድ ላይ መኖር አትችሉም አሉ ። እኔም እሷን በሥርግ ለማግባት አላቅማማሁም ግን ሠርጉ ምን ያህል ትልቅ ይሁን አይሁን የሚለውን ከሷ ጋር ብንሰማማም ከቤተሰቦቿ ጋር ልንግባባ ግን አልቻልንም ። ቢሆንም መጠነኛ ሠርግ ተደረገና ተጋባን ። ከዛም ልጅ ተወለደ ። የምታዩት ልጅ ገና አንድ አመቱ ነው ። ገና የልጇን ሽታ ሳልጠግብ ነው ከሥራዬ ላይ ታስሬ የመጣሁት ። ደርግ ፅህፈት ቤት በተደጋጋሚ ሰለተገረፍኩ ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ አካለ ስንኩል ሆኛለሁ ። የእግሮቼ ጣቶች ተቆራርጠዋል ። በእግሬ መቆምም አዳግቶኛል ። እግዜር ብሎ ከተፈታሁ እንዴት እንደምሆን አላውቅም ።ቤት ለመስራት ዕቅድ ነበረን ። እንዴት አድርጌ በዚህ ሁኔታዬ ተራውጩ ቤት እንምሰራ አላውቅም ።

ልጄንስ እንዴት አድርጌ ነው የማሳድገው? ጥፋቴ ሆኖ የተገኘው የሠራተኛው ማኅበር ተመራጭ በመሆኔ ነው ።የኢሕአፓ አባል ነህ ብለው ቀጠቀጡኝ ። እሄው እንደምታዩት አደረጉኝ ፣ ብልቴን ቀጠቀጡት ፣ የጀርባዬን አጥንት ሰባበሩት ፣ ነገ ምን እንደሚያደርጉኝ አላውቅም ። ልጄስ ምን ይሆናል ? ሚስቴስ ? ብሎ በእንባ ታጠበ ። ስቅስቅ ብሎ ለረጅም ጊዜ አለቀሰ።

የእሱ ስቃይ በዚህ አላለቀም ። ጣቶቹ ዓይኑ እያየ ከመገረፍ በመጣ ቁስል ተቆራርጠው ወደቁ ።ግን ይህም ሆኖ ስቃዩን ሁሉ ችሎ ሁላችንን ሲያፅናና የነበረ ጀግና ነው ። ሁላችንም እንወደዋለን ፣ እሱን እያየን ጥንካሬን ፣ ብሩሕ ተስፋን እናልማለን ፣ እንደሱ ፍቅረኛ ይዘን ታሪካችንን የምንተርክበት ወቅት እንመኛለን ። እንደሱ በተስፋ መኖርን እንመኛለን። እሱን እንወደዋለን ።

አንድ ቀን ወደ ማታ ላይ እንደተለመደው ከደርግ ፅህፈት ቤት የገዳዮቹ መኪና የሚገደሉትን እስረኞች ለመውሰድ መጣች ። ስም ይጠራ ጀመር ። የእሱ ስም የመጀመሪያው ነበር ። ተነሳ ፣ ቆመ ፣ ፈገግ አለ ። የመጨረሻው ቀን መድረሱን በማይረሳ ፈገግታው አበሰረን ።ሰለራሱ ስቃይ ልቅሶ ወይም ሀዘን አልታየበትም። ምንም አላለም ። በኪሱ የነበረውን ንብረቶቹን ሰጠን ። ከበሩ ለመውጣት በቆሰለ እግሩ እየተውተረተረ ዘወር ብሎ እንዲህ አለን ።

“የሠርግ ቀለበቱን አውጥቶ እሁድ ስትመጣ ለዝናሽ መልሱላት ብሎ ሰጠን ። አንድ ነገር እለምናችኋለሁ ። የምግብ ሰሃን እንዳትመልሱ በድንገት መኪና ውስጥ ገብታ ትሞትብኛለች ። በሰማይ ቤት እንደምጠብቃት ንገሩልኝ ። እዚህ ምድር ላይ ያልጨረስነውን ፍቅር እዛ እንጨርሰዋለን። በጣም እንደምወዳት ንገሩልኝ። “ ብሎ ሳይጨርስ እየገፈታተሩ አወጡት ። “እሁድ ለት ተጠንቀቃችሁ ንገሯት!!”። እያለ እየጮኸ ሄደ ።

በዚህ ምክንያት ነው ፍርደኛና ሐኪም ቤት አካባቢ ሃዘን የገባው ።በዛ የምንገኝ ሁላችንም የሙት ሰው አደራ አለብን ። የፍቅር ጥሪውን ከመርዶው ጋር እንዴት ነው የምንነግረው ? ሁላችንም ተከዝን ። የምግብ ሰሐኑ ሲመጣ የሚበላው ጠፋ ። በውቅቱ እዛው ታስሮ ለነበረ አንድ ሶማሌ ሰጠነው ። አዲስ አበባ በፋሽሽቶች ጥይት ሌሊቱን ፀጥታዋ ደፍርሶ ነበር ። የትኛዋ ጥይት ትሆን እሱን የገደለች ? እያልን ስናምሰለስል ነበር ።

አይደርስ የለ እሁድ ደረሰ። እንደተለመደው እስረኞችን ለመጠየቅ ከተሰለፉት ሰዎች እሷ የመጀመሪያ ሆነች ። ሁላችንም ማልቀስ ጀመርን ። ማን ሄዶ ይንገራት? ማን ልብሱን መልሶ ይስጣት ? ቸገረን ። እንደተስማማንበት ቤተሰቦቻችን ሲመጡ አጠገቧ እንዲከቧት በምስጢር ተናገርን ። መከበቧን ካወቅን በኋላ ቀለበቱን ሰጠናት ። አላመነችም ። ደነገጠች ። ከበዋት የነበሩት ያዟት ። ለቅፅበት ትንሽ ካሰበች በኋላ

"ካሱሱሱሱ. . . . . . . . . . . . . . . . . . !!!" ብላ ጮሃ የከበቧትን ሰዎች ገፍትራ መሬት ወደቀች ።

ለባሏ ሞት ስታለቅስ ብትገኝ እሷም ትታሰራለችና ሰዎች ደጋግፈው ይዘዋት በድብቅ ወደምታለቅስበት ወሰዷት። እኛም ወደ ውስጥ ተመልሰን ። የማይታወቀውን ዕጣ ፋንታችንን እንጠብቅ ጀመር።

# በሰላም ያገናኘን አለ

የማትቀረዋ ሰአት ፤
አንዳንዴ በድፍረት እየናቃት፤
አልፎ አልፎ እየራደ በፍርሃት ፤
ሲጠብቃት ።

ብትመጣ የሚጠብቀውን ሞት አዝላ ፤
በምድር ሲኦልን ተመስላ፤
ተዘጋጅቶ እንዳልጠበቃት ፤
በደስታም አላቀፋት ፣ በስሜት አልፈነደቀ፤
በፍርሃት ተሸማቀቀ።

መንፈሱን በዜማዋ ቃኝቶ ፤
ቀለበቱን ከጣቱ ፣ ሰዓቱን ከእጁ ፈትቶ፤
ሃብሉን ከአንገቱ አውልቆ ፤
እላቂ ጨርቁን አጥልቆ ፤
ጸጉራም ደረቱን ለጥይት ፤ለእርሳስ አሰናድቶ፤
ስቃዩን ቀድሞ እያቃሰተ፤
በእስሩ ላይ እየሞተ ፤
ሲጠብቃት፤
የማትቀረዋ ሰአት ፣
በወታደር ጫማ ሹክሹኩታ ፤
የእስር ቤት ውስጥ ኡኡታ ፤
በፍርግርግ መስኮት የስም ጥሪ ፤
ትውልድን ለሞት አሰማሪ ፤
ታጅባ ብትመጣ ፤
አቤት !
የብረት በሩ ሲከፈት ፤
ማን ያውቃል ያቺን ሰአት !?
ከእሱ በቀር ፤
ያቺን የሕይወትና ሞት ዳር ድንበር ።

ደግሞ ጠንካራ ገመድ በወጣት ደም የተዛበ፤
ጭካኔን የዘገበ ትውልድን የታዘበ።

እና . . . . . .
ባይተዋሩ ቀጠሮ ሞት ፣
እንደቀጠሩት እንግዳ ሳይጣደፍ ፤ እንደ አልፎ ሂያጅ ተዝናንቶ፤
ቢመጣበት ፤
ሲጠብቅ ውሎ እንዳላደረ ፤
እንደበቱ ተሳሰረ።

የጠበቀው እንግዳ ፤
ሆኖበት ባዳ ፤
ዞር ብሎ፤
የእስር ቤት ጓዶቹን እያስተዋለ ፣
ቋንቋ እንኳ ወንብዶበት " በሰላም ያገናኘን " አለ።
ምስኪን ።

በድሉ ዋቅጅራ ከደብረ ማርቆስ እሰር ቤት በቀይ ሽብር ሊገደል ስሙ ሲጠራ ጓደኞቹን "በሰላም ያገናኘን" ብሎ የተሰናበተውን የኢሕኣፓ አባል ታሪክ በፈጠረው ስሜት የተጫረ። ፍካት ናፋቂዎች ከሚል መፅሐፍ የተገኘ

ሰለ ካሱ የሚያስብ ሁሉ በሰላም ይከረም

በልጅግ አሊ